# ሕግን እየጣሱ ሕግ እናስከብራለን በአንድነት ፓርቲ ውስጥ

አንድ ፓርቲ የሚተዳደርበት ህግና ደንብ አለው ። አባላቱም ለመተዳደሪያ ደንቡ ፍፁም ተገዢ ሆነው ፓርቲው ለቆመለት ዓላማና ግብ ይታገላሉ ። በቅርቡ በአንድነት ፓርቲ ውስጥ የተፈጠረውን ችግር አስመልክቶ ዝም አንልም / ህግ ይከበር የሚባልው ስብስብ የሚያደርገውን ፀረ አንድነት ፓርቲ እንቅስቃሴን ስከታተል ቆይቻልሁ ። ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ለችግሩ ጭብጥ ሊሰጡ የሚችሉትን አንቀጾች መጥቀስ አስፈላጊ በመሆኑ የተወሰኑትን እነሆ ። አንቀፅ 4.5. አሉባልታን ፣ ሥርዓትና ደንብን ያልተከተለ አሰራርን ፣ የግለሰብ ፈላጭ ቆራጭነትንና አፍራሽ ቡድናዊነትን መታገል ፣ አንቀፅ 7.5 . የፓርቲውን ዓላማ ፣ አንድነትና አሰራር ከሚጎዱ ማናቸውም እንቅስቃሴዎችና የስነ ምግባር ጉድለቶች መቆጠብ ፣ አንቀፅ 7.6. ለፓርቲው ታማኝ መሆንና ሚስጥር መጠበቅ ። ለምሳሌ አቶ ታምራት ታረቀኝ የፓርቲው ስራ አስፈፃሚ አባል በነበሩበት ወቅት በአንድ ስብሰባ ላይ ያቀረቡት ሃሳብ በአብላጫው የስራ አስፈፃሚ አባላት ውድቅ ሲሆን በማግስቱ ፓርቲው ሲወያይበት የነበርውን ሚስጥር በጋዜጣ ላይ እንዲወጣ አደረጉ እሳቸውም ይህንን ማድረጋቸውን አምነዋል አቶ አምሃ ዳኜም እንዲሁ ተመሳሳይ ድርጊት ፈፅመው ተገኙ ። በዚህም ሳያበቁ በተደጋጋሚ ፓርቲውን ሊጎዳ የሚችልን ድርጊት ሲፈፅሙ ከቆዩ በኋላ ከፓርቲው ታግደዋል ። የግለሰቦቹ ከፓርቲው መታገድ የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ ተከትሎ እስከሆነ ድረስ ስህተቱ ምኑ ላይ ነው ? የአገሪቱ ሚዲያ ብቸኛ ባለቤት የሆነው ወያኔ / ኢህአዴግም ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ማጥላላተና ከህዝቡ ጋር ሆድና ጀርባ እንዲሆኑ የሃሰት ፕሮፖጋንዳውን በሰፊው ተያየዞት እንሚገኝ ይታወቃል ። አገዛዙ ለተያያዝው ዘመቻም ያመች ዘንድ የፓርቲውን የውስጥ ጉዳይ በየሚዲያው ላይ ማስፈርና ፓርቲውን ሊጎዳ የሚችል ስራ መስራትና ፀረ አንደነት ፓርቲ እንቅስቃሴን ማካሄድ በምንም መስፈርት ዴሞክራሲ ሊሆን አይችልም ። በመሆኑም ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ማን ነው ? መሰረታዊ ችግሮቻችንስ ምንድናቸው ? በሚሉት ነጥቦች ዙሪያ የግል አስተያየቴን ለመሰንዘር እሞክራልሁ ።

በታዘብኩት መሰረት አራት እንደ ዋና ችግር ተደርገው በሚነሱ ነጥቦች አስተያየቴን እሰነዝራልሁ

1. አብላጫ ድምፅን በተመለከተ

በአንድ ፓርቲ ውስጥ አንድ ሃሳብ በአባላቱ ከተንሸራሸረ በኅላ በአብላጫ ድምፅ ይወሰናል የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ እንዲህ ይላል አንቀፅ 4.4. በፓርቲው ውስጥ ሃሳብን በነፃነት የማንሸራሸር መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ለብዙኀን ውሳኔ ተገዥ መሆንና የፓርቲ መዋቅርን ጠብቀው የሚተላለፉ የበላይ አካላትን ውሳኔና መመሪያዎች ማክበርና ተግባራዊ ማድረግ ይህ አሰራር በአለም ላይ ባሉ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲዎች ወይም አገሮች ውስጥ ሲሰራበት የኖረና አሁንም ድረስ ያለ ነው ። በፓርቲው ውስጥ የሚንሸራሸረው ሃሳብ ለአገር እና ለወገን የሚጠቅም ሆኖ እያለ ግን አብላጫ ድምፅ ባለማግኘቱ ብቻ ውድቅ የሚሆንበት ጊዜ በጣም ብዙ ነው። ለምሳሌ በስዊዘርላንድ አንድ ህግ የሚወጣው ህዝቡ ድምፁን ( ረፈረንደም) ከሰጠ በኋላ ነው ። ማለትም የህዝብ ውሳኔው ድጋፍም ይሁን ተቃውሞ ከ 50% በላይ ከሆነ እንደ ህግ ይፀድቃል ። የአሜሪካኑን የጤና ዋስትና ለሁሉም የሚለውን ህግ ለማፀደቅ ያለውን ችግርም እንደ ምሳሌ ማቅረብ ይቻላል እስከዛሬም እየወደቀና እየተነሳ አሁን ያለበት ደረጃ ደርሷል ።

ይህ ህግ ተቀባይነት እንዲኖረው ሕጉን ባቀረበው ፓርቲም ይሁን በተቃራኒው ፓርቲ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ለማሳመን ከፍተኛ የቅስቀሳና ድጋፍ የማሰባሰብ ስራ ይሰራል ። በአንድነት ፓርቲ ውስጥም የተከሰተው ይሄው ነው ። ዶ/ር ሽመልስ ተክለፃድቅ በአንድ ቃለ-መጠይቅ ተጠይቀው ሲመልሱ እንደሰማሁት በአንድ ስብሰባ ላይ መድረክን በተመለከተ አጀንዳ ይቀረብና በምክር ቤቱ አብላጫ ድምፅ ሳያገኝ ቀርቶ ይወድቃል ። በሌላ ጊዜም እንዲሁ በድጋሚ የመድረክ ጉዳይ በአጀንዳነት ቀርቦ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር አበሮ መስራቱ አስፈላጊነቱ አብላጫ ድምፅ ያገኛል  አጀንዳ አቅራቢዎቹም በመጀመሪያ ሲያቀርቡት በመውደቁ ሳያኮርፉ ወይም ሃሳባችን እንዴት አይሰማም ብለው ችግር ሳይፈጥሩ ውስጥ ለውስጥ ከመድረክ ጋር መስራት አስፈላጊነቱን በማሳምን በሁለተኛው ዙር አብላጫ ድምፅ እንዲያገኝ አድርገዋል ። ይህም የሰለጠነ ፖለቲካና በአለም ላይ ባሉ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲዎች ውስጥ ያለ አካሄድ ነው ። ዶ/ር ሽመልስም የአብልጫ ድምፅን ውሳኔ አልቀበልም ብለው ይመሩት የነበርውን ስብሰባ ረግጠው እንደወጡ ተናግረዋል ። ስበሰባውን ረግጠው መውጣታቸው መብት ቢሆነም ለፓርቲው ውሳኔ አልገዛም በማለት ለፓርቲው ህግና ደንብ ለመገዛት ፈቃደኛ አለመሆናቸውን አሳይተዋል ።

የሚያሳዝነው በተለያየ የፓርቲው ስብሰባ ላይ አነስተኛ ድምፅ ያለውን ሃሳብ ያልደገፉትን የብሄራዊ ምክር ቤት አባላት ሎሌ በገንዘብ የተገዙ እያሉ መሳደብን እነ ፕሮፌሰር መስፍን ከየት አመጡት ? ሁላችንም እንደምናስታውሰው የቅንጀት መሪዎች ከተፈቱ በኋላ መታሰር እንደ ጀግንነት/ ኒሻን ተቆጥሮ ፓርላማ የገቡ የቅንጅቱ አባላትን የማግለል ስራ እየሰሩ ነው ብለው ሲከሱና አስተሳሰቡን ሲያውግዙ በተደጋጋሚ ተደምጠዋል ። አንድነት ፓርቲንም በጋር ስትመሰርቱ ጥርት ያለ እምነት ኖሯችሁ ፓርላማ የገባ ያልገባ የሚለውን አስተሳሰብ ጥላችሁ ነው ። ታድያ ዛሬ እርስዎም ሆኑ ዝም አንልም ቡድን እንዴት ተመልሳችሁ ፓርላማ ገብተው የነበሩ የቅንጅቱን አባላት ለመሳደብ ወሰናችሁ ? እነዚህ ግለሰቦች አናሳ ድምፅ ያልውን ሃሳብ ማለትም የዝም አንልምን ደግፈው ቢሆን ኖሮ ፓርላማ መግባታቸው እንደ ድክመት ተቆጥሮ ላይዘልፉ ነበር ።

ሌላው በጣም የሚያሳዝነው ለአብላጫ ድምፅ መገዛት የዴሞክራሲ መለኪያ አይደለም ሲባልም እየተደመጠ ነው ።  የፓርቲው መተዳደርያ ደንብ እንዳለ ሆኖ በአንድ ፓርቲ ውስጥ የአብላጫው ደምፅ ውሳኔ ካልተከበረና በጋራ ወደ አፈፃፀሙ ካልተሄደ ስራ እንዴት መስራት እንደሚቻል ቡድኑ የራሱ የሆነ ፍልስፍና ካልው በግልፅ ቢያስቀምጠው መልካም ነው ። አለበለዚያ አካሄዱ ስርዓት አልበኝነትን በፓርቲው ውስጥ እንዲነግስ መፍቀድ ነው ። ይሄ ደሞ ስራ ሳይሰሩ እንዲሁ ሲላፉ መኖር ማለት ነው ። ለአብላጫው ድምፅ ውሳሌ ላለመገዛት እናም የዴሞክራሲ መለኪያ አይደለም ሲሉ የአፍሪካ አምባገነኖችን በምሳሌነት ይጠቅሳሉ ። ይህ አባባል ማንን ለማደናገር ይሆን ? የአፍሪካ አምባገነኖች ፓርቲያቸውንም ሆነ ፓርላማቸውን ያዋቀሩት ኢ-ዴሞክራሲያዊ በሆነና የነሱን ሃሳብ በሚደግፉ ግለሰቦች ነው ። አንድነት ፓርቲን በአንድነት ስትምሰርቱ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ተከትላችሁ እንደሆነ ተከታትለናል ። አመራሮቻችሁንም ስትመርጡ እንዲሁ ነበር እናም ምኑን ከምኑ ለማመሳሰል እንደሞከራችሁ ግልፅ አይደለም ። እንደ መከራከሪያነት ያቀረባችሁት ሃሳብም ሚዛን አይደፋም።

1. ብርትኳንን በተመለከት

ከሁሉም በላይ የሚገርመው ወ/ት ብርትኳንን በተመለከተ የሚቀረበው ክስ ነው ። በይዘቱ የወረደ ለአድማጭም ሆነ ለአንባቢ በጣም የሚያሳዝን ነው ። የሚነሱት ነጥቦች ምን እንደነበሩ መልሼ ለማፃፍ ህሊናዬ እምቢ ስላለኝ ትቼዋለሁ ። በእኔ አመለካከት የሚቀረበው ክስ ከእውነት የራቀ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ያለበኝ አይመስለኝም ። አንድ ሰው ምንም ያህል የስልጣን ጥም ቢኖረው እራሱን ለዛ ስልጣን ለማብቃት ማድረግ ያለበትን ነገር በሙሉ ያደርጋል እንጂ በፓርቲው ውስጥ መቀጠል ያሰበ ሰው ባደባባይ ያውም እንደ እናንተ አባባል የብርትኳን ደጋፊዎች ባሉበት ይህን አሉ ብሎ መክሰስ የመጨረሻ የሚያሳዝንና ምን አይነት ሰዎች እንደሆንን ስለራሳችን ደካማ ባህሪ እየተናገረን እንደሆነ አለማስተዋላችን ነው የአንድነት ፓርቲ ምስረታን ቪዲዮ ተመልክቼዋልሁ አመራሩም ከተመረጠ በኋላ በግለሰቦቹ መካከል ይታይ የነበረው አንድነትና ደስታ በምርጫው ውጤት ተከሳሾቹ ስለማዘናቸው ወይም ስለመከፋታቸው የሚጠቁም ነገር አይታይም ። ስለዚህ ለማስጠላት ያደረጋችሁት ሙከራ አንባቢ / አድማጭ እናንተን እንዲታዘብ ዓላማችሁም ምን እንደሆነ እንዲጠራጠር በር ከመክፈት በዘለለ ያመጣው ነገር የለም ። የሚገርመው ነገር ደሞ እራሳችሁን ለወ/ት ብርትኳን ከማንም በላይ አሳቢ እና ተቆርቋሪ አድርጋችሁ ከማቅረባችሁ ውጪ በተግባር እስዋ የምትፈታበትን ዘዴ አለመፈየዳችሁ ነው ። በአንድነት ፓርቲ ላይ ያለ ምንም ፈቃድ ሰልፍ ስታደርጉና ቢሮ መስበር ደረስ ደፍረቱ ሲኖራችሁ ብርትኳን ትፈታ ብላችሁ ሰልፍም ሆነ ሌላ ነገር ስታደርጉ አለመታየታችሁ የምታቀርቡትን ክስ ውድቅ ያድርገዋል ። በቂ ነው አይደለም የሚለው ሌላ ነገር ሆኖ ከሰላማዊ ሰልፍ ጀምሮ እስከ ቃሌ ዝግጅት ድረስ አሁንም ብርትኳን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እድትፈታ የሚጠይቅ ፒቲሽን አዘጋጅቶ እያስፈረመ የሚገኘው ተከሳሹ ብዙሃኑ የአንድነት ፓርቲ ነው ። እዚህ ላይ አንድ ነገር ልጨምርር ሰሞኑን ሁለት የእምቢ ዝም አንልም ቡድን አባላት ቃለ መጠይቅ ተደርገው ነበር ። አቶ የሸዋሰው ሲናገሩ ፒቲሽን ተከሳሹም እኛም አዘጋጅተናል ህዝቡም የኛን ፒቲሽን በከፍተኛ ሁኔታ እየፈረመ እንደሁነ ሲነግሩን በሌላ በኩል ደግሞ ዶ/ር ሽመልስ ፒቲሽኑን የአንድነት ፓርቲ ቢያዘጋጀውም ለብርትኳን እስከሆነ ድረስ ማንም ያዘጋጀው በሚል በከፍተኛ ደረጃ የዝም አንልም ቡድንም እያስፈረመ እንደሆነ ተናግረዋል ። አቶ የሸዋሰው እውነቱን ለመናገር ወኔ ለምን አነሳቸው ? በዚህ አጋጣሚ ብርትኳን የሁሉም ኢትዮጵያዊ የትግል አርማችን ነች ። ስለዚህ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በግልም ይሁን በቡድን ብርትኳን እንድትፈታ ጥረት ያድርግ ዘንድ ጥሪየን አቀርባለሁ ።

2. የሞያ ሰራተኞች ከስራ ገበታቸው መታገደን በተመለከተ

አንዱ ሌላው እንደ ችግር እየተጠቀሰ ያለው ነገር አንድ የፅዳት ሰራተኛና አንድ ፀሓፊ ያለአግባብ ከስራ ገበታቸው ተባረሩ የሚል ነው ። ግለሰቦቹ የተባረሩት ደሞ ለረጅም ግዜ በህመም ምክንያት በስራ ገበታ ላይ አለመገኘትና በስራ መደራረብ በተፈጠረ አለመግባባት እንደሆነም እራሳችሁ አምናችሁ የገለፃችሁት እውነታ ነው ፓርቲው የፈለገውን ሰው ቀጥሮ የማሰራትም ሆነ ከስራ ገበታው የማሰናበት መብት አለው ። አንድነት ፓርቲ ሁለት የሞያ ሰራተኞችን ለምን አባረር ብሎ ድርጅቱን ማወክና በውስጥ ችግር ተተብትቦ እንዳይሰራ ማድረግ ትልቅ ስህተት ነው ። ወያኔም ህዝብ ላይ ያለማንም ተው ባይነት ወይም ተቃዋሚ የፈለገውን እንዲያደርግ መፍቀድ ነው ። አስተዋይ የሆነ ግለሰብ የፓርቲውን አስተዳደራዊ ውሳኔ ተቀበሎ ወደ ዋናው ችግርና ዴሞክራሲያዊ ሰርዓትን ወደ ማምጣቱ ትግል ላይ ያተኩራል እንጂ ፓርቲውን በውስጥ ሽኩቻ

አስሮ ለማስቀመጥ ጥረት ማድረግ የሚያሳዝን ነው ። ከአሁን በፊትም በተለያዩ ፓርቲዎች ታይቷል ወያኔ የተወሰኑ ሰዎችን ችግር እንዲፈጥሩ ሁኔታዎችን እያመቻቸ ፓርቲ ለማፍረስ ጥረት እንድሚያደርግ ይህንንም ከዛ ለይቼ አላየውም

3. መድረክን በተመለከተ

ዝም አንልም ቡድን አባላትም መድረክን በመቀላቀል ላይም የጠራ አቋም የላቸውም።የተወሰኑት በሌላ ችግር እንጂ ከመድረክ ጋር አብሮ ለመስራት መነሳቱ ችግር እንደሌለው ሲጠቅሱ የተወሰኑት ደሞ ከመድረክ ጋር አብሮ ለመስራት መነሳትን እንደ ጥፋት ወይም ክህደት ጭምር አድርገው ሲወስዱት ይደመጣል ። ቅንጅትም ሆነ የቅንጅት ወራሽ የሆነው አንድነት የኢትዮጵያ ህዝብ ችግር ጥልቅ እና ሰፊ መሆኑን ተቀብሎ በዛች አገር ላይ ብሄራዊ እርቅ እንዲወርድ ብሎም አገዛዙን በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመቀየር ከተለያዩ ብሄራዊም ይሁኑ ህብረብሄራዊ ድርጅቶች ጋር መስራት ጠቃሚ እንደሆነ በደንብ አስቀምጦታል። ስለዚህ ከተነሳበት አላማ አንፃር አንድነት ከመድረክ ጋር ለመስራት ሲወስን ችግሩ ምኑ ላይ እንደሆነ አልታየኝም ። ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ተቀናጅቼ ልስራ ሲባል ደሞ ሌሎች የአንድነትን ፕሮግራም እንዳለ ይቀበላሉ ማለት አይደለም እንደዚህማ የምናስብ ከሆነ ቅንጅትም ሆነ ህብረት መመስረት ላይቻል ነው ። የተቃዋሚዎች ህብረት / መቀናጀት ከሌለ የሚመቸው ደሞ አገዛዙን ነው ። በተናጠልም ፓርቲዎቹን ለማጥቃት እድል መስጠት ነው ። የኢትዮጵያ ችግርም አንዳንድ የዋሆች እንደምናስበው እንዲህ በቀላሉ የሚፈታ አይደለም ።

አንድነት መድረክን በመቀላቀሉ እስካሁን ሁለት አበይት ስራዎችን አከናውኗል ።

a. የተለያዩ ድርጅቶች በፕሮግራማቸው ላይ ያልውን የእስከ መንገንጠል ፕሮግራም እንዲጥሉ አስችሏል
b. የመድረክ መመስረት ለአገዛዙ እራስ ምታት ሆኖበታል ምክንያቱም በአሁኑ ሰዓት እየተሰራ ያለውን ድራማ ( የስነምግባር ስምምነት ) እምቢ ለኢትዮጵያ አይበጅም እናንተ ባመጣችሁት አጀንዳ ብቻ ሳይሆን እኛም የራሳችን አጀንዳ አለን ብለው ስርዓቱን ወጥረው ለመያዝ ችለዋል ወያኔም የተቃዋሚዎች ህብረት እንደፈለገ እንዲፈነጭ ስላልፈቀደለት መድረኩን ለማፍረስ ተያይዞት ያለውን ዘመቻ ሁላችንም ታዝበናል እያየንም ነው። ወደፊትም የመድረክ መጠናከር ወሳኝነት አለው ። በመድረኩ ዙሪያ የተሰባሰቡ ፓርቲዎችም የተወሰኑ ጥቂት የፕሮግራም ልዩነታቸውን በሒደት በማጥበብ ጠንካራ ስራ ሊሰሩ ስለሚችሉ ድጋፋችንን ልንሰጣቸው ይገባል ።

4. አቶ ስዩና ዶ/ር ነጋሶን በተመለከተ

የግለሰቦቹ ወደ አንድነት ፓርቲ መግባትም እንደ ችግር ተወስዶ በዝም አንልም ቡድን ሲተች እየተደመጠ ነው ። ወቀሳውም ይለያያል ተመሳሳይ አቋም አይታይባቸውም ለምሳሌ አቶ የሸዋሰው የነ ስየ ወደ አንድነት መግባት አግባብ እንዳልሆነ ከነበራቸው ታሪክ ማለትም ከአገዛዙ ጋር በመስራታቸው በከፍተኛ አመራርነትም ያገለገሉ በመሆኑ ለአንድነት ፓርቲ አይጠቅሙም እንዳውም አንድነትን ይጎዳሉ ብለው እንደሚቃወሙ ተደምጠዋል ። በሌላ በኩል ዶ/ር ሽመልስ ተክለፃድቅ ደሞ የሚቃወሙት አሁን እኛ ስንባረር የነ ስየ ወደ ፓርቲው መግባት ትክክል እንዳልሆነ ከአሁን በፊት እንዳውም እሳቸው አቶ ሰየን ወደ አንድነት ፓርቲ እንዲገቡ ሲጥይቁ የመጀመርያ ግለሰብ መሆናቸውን ነገር ግን አቶ ስየ በወቅቱ ፈቃደኛ እንዳልሆኑ አስተያየታቸውን ሰተዋል። አቶ ሰየን የጠየቁበት ምክንያትም ግለሰቡ አገዛዙን እየታገለ በመሆኑ ካሳየውም በሳል እንቅስቃሴ የተነሳ እንደሆነ የኋላ ታሪካቸውም ሊጎትታቸው እንደማይገባ እምነታቸው እንደሆነ ተናግረዋል ። በእሳቸው ግምትም ወ/ት ብርትኳንም ግለሰቦቹን አነጋግራቸው እንደነበር ነው የተናገሩት

ግለሰቦቹ ወደ አንድነት ፓርቲ ቢገቡ ለትግሉ የራሳቸውን ድርሻ ሊወጡ እንደሚችሉ በአብዛኛው የፓርቲው አመራርም ሆነ ላዕላይ ምክር ቤት ተመሳሳይ አመለካከት አለ ዝም አንልም ቡድንን ጨምሮ ። ችግሩ እኛ ስንባረር እንዴት ይገባሉ እንጂ ሊያበረክቱ በሚችሉት አስትዋፅኦ ላይ ምንም ጥርጣሬ የላቸውም ። እነዚህ ግለሰቦች ለኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ለአንደነት ፓርቲ ሊያበረክቱት የሚችሉትን አስተዋፅኦ እኛ ስለተባረርን አንቀበለውም ብሎ ለማጣጣል መሞከር እና ሌላ ትርጉም መስጠት ግን እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አይነት ፖለቲካ ስለሚሆን ያቀረባችሁት ክስ በኔ በኩል ውድቅ ነው ። ዝም አንልም ውስጥ ያሉ ግለሰቦች እነ አቶ ሰየ አንድነትን እንዲቀላቀሉ በጋበዟቸው ጊዜ ተቀላቅለው ቢሆን ኖሮ ትክክል ሊሆን አሁን ደሞ የአንድነት ፓርቲ በድጋሚ ጋብዟቸው እነሱም አስበውበት ሲቀላቀሉ ስህተት የሚሆነው በምን ሂሳብ ይሆን ?

በስተመጨረሻም ለማለት የምፈልገው የአንድነት ፓርቲ በዲሲፒሊን ጉድለት በተባረሩት የብሔራዊ ምክር ብሬቱም ይሁን የስራ አስፈፃሚ አባላት የተነሳ ስራው ሳይስተጓጎል ስራውን በሚገባ ሲሰራ ቆይትዋል አሁን በቅረቡም በጎደሉት ምትክ ብሄራዊ ምክር ቤቱነም ሆነ ስራ አስፈፃሚውን ያሟላ ስለሆነ ወደፊት የተሻለ ስራ እንደሚሰራ አምናልሁ ። ከፓርቲው የተውገዱትም አባላት የፓርቲውን መዋቅር ጠብቀው ውሳኔው ትክክል አለመሆኑን ያሳዩበት ጊዜ የለም ይልቁንም ሚዲያ ችግሩን ይፈታው ይመስል የተሳሳት ጎዳናን ነው የመረጡት ። ዝም አንልም ቡድንም አንድነትን ለማናጋት የሚያስችለውን የስም ማጠፋትም ሆነ ሌላ ነገር አድርጓል ። ከዚህ ሌላ የሚጨምሩት የስም ማጥፋት ዘመቻ አይኖርም ይሄንንም ሲደክማቸው እንደሚትውት እሙን ነው ። እንደ እኔ አመለካከት ከሆነ አሁንም ቢሆን ለተሰራው ጥፋት ይቅርታን በመጠየቅና እራስን ለፓርቲው ህግና ደንብ ለማስገዛት ቆርጦ በመነሳት ከአንድነት ፓርቲ ጋር መቀጠል ይቻላል ካልሆነ ያላቸው አማርጭ ሌሎች ፓርቲዎችን መቀላቀል ወይም የራሳቸውን አዲስ ፓርቲ አቋቁሞ አገዛዙን መታገል እንጂ ከአንድነት ጋር የጀመሩት ግብግብ ያበቃለት ጉዳይ ነው ።

አሁን በቅርቡም የጀመራችሁት የወያኔ የፕሮፖጋንዳ ማሽን በሆነው ኢቲቪ ፊት ለፊት ለመደባደብም ሆነ ስርዓቱ በተቃዋሚው ላይ ለሚያደርገው ዘመቻ ድጋፍ ማድረግ ማንን ለመጥቀም እንደሆነ የምታውቁት እናንተ ናችሁ። የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ከዚህ አካሄዳችሁ እንደማይጠቀም ለማንም ግልፅ ነው ። ማንንስ ብትተማመኑ ነው ለመደባደብ እና ቢሮ ለመስበር የደፈራችሁት ?

አንዳንዶችም አንድነት ፓርቲ እንዴት ፓሊስ ይጠራል ሲሉ ይደመጣሉ ። በመጀመሪያ የሚጠራው ፓሊስ ለመምጣት ፈቃደኛ ባለመሆኑ አልመጣም ምክንያቱም ዝም አንልሞችን ከቦታው ዞር እንዲሉ እንዳይረበሹ ማድረግ ከአገዛዙ ጥቅም አንጻር ስለማይፈለግ ነው ። ችግሩን ለመፍታት ፓሊስ መጥራት ወይስ ወያኔ ፊት መደባደብና የህዝብ ስሜት ማቁሰል እንደሚሻል ለመለየት አስቸግሮ አይመስለኝም ። አንድነት ፓርቲ ፓሊስ መጥራቱን እንደጥፋት ለማቀረብ አንዳንድ ሰዎች የሚሞከሩት ስህተትና ፀጉር መሰንጠቅ ነው ምክንያቱም የቀረው አማራጭ የማይጠቅምና በብዙ መልኩ ጎጂ በመሆኑ ። ዝም አንልም ቡድን አንድነት ምን አይነት ፓርቲ እንደሆነ ግለሰቦቹም እነማን እንደሆኑ ለህዝብ እናሳውቃለን ህዝብም እንዳይመርጣቸው እንሰራለን ስትሉ ትደመጣላችሁ ። ይሄ ማለት ከወይኔ የተሻለ ተቃዋሚ ስለሌለ ወያኔን ምረጡ ይመስላልና ትክክል ነው ብላችሁ ካመናችሁ መቀጠል መብታችሁ ነው። ፍርዱን የሚሰጠው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው በኢቲቪ ( የወያኔ ፕሮፖጋንዳ ማሽን ) ብቅ እያላችሁ ህዝብን አታሳዝኑ እምቢ ብላችሁ ከገፋችሁም ምን ያህል እንደምትጓዙ ወደፊት የምናየው ይሆናል ። የኢትዮጵያ አምላክ አገራችንን ከጥፋት ይጠብቅ አሜን ።

ብርትኳን ትፈታ !!!

ዜግነት ከኦስትሪያ